በትግራይ ክልል ግብርናና ተፈጥሮ ሃብት ቢሮ/ FSRP/ በ 2018 ዓ.ም በፀደቀውን የግዥ ዕቅድ መሰረት በትግራይ ክልል በ FSRP home solar light (Procurement ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ ውስጥ የተጠቀሱት ዕቃዎች መግዛት ስለሚፈልግ የመወዳደሪያ ሀሳብ እንድታቀርቡ ይጋብዛል ::

የተለቀቀበት ቀን: ረቡዕ የካቲት 4, 2018 (24 ቀናቶች)
መዝግያ ቀን: ሶኒ የካቲት 9, 2018 03:30 ጥዋት (ተዘጋ)
የጨረታ ማስከበርያ ዋጋ:
ቦታ:መቐለ
የጨረታ ደኩመንት ዋጋ:
ጨረታ ሚከፈትበት ቀንና ሰዓት: ሶኒ የካቲት 9, 2018 04:00 ጥዋት
ምድብ: ኤሌክትሪካልን መሳርሕታትን መለዋወጢን/ ኤሌክትሮኒክስ መሳርሕታትን መለዋወጢን/ ኤሌክትሮ-መካኒክስ ኣቑሑትን ግልጋሎትን/

የግዥ መለያ ቁጥር /1/2018-ዓ.ም

ጉዳዩ፦ ለሶስት ግዜ የወጣ ለዕቃዎች ግዥ የመወዳደሪያ ሀሳብ እንዲያቀርቡ

በትግራይ ክልል ግብርናና ተፈጥሮ ሃብት ቢሮ/ FSRP/ በ 2018 ዓ.ም በፀደቀውን የግዥ ዕቅድ መሰረት በትግራይ ክልል በ FSRP home solar light (Procurement ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ ውስጥ የተጠቀሱት ዕቃዎች መግዛት ስለሚፈልግ የመወዳደሪያ ሀሳብ እንድታቀርቡ ይጋብዛል :: መስሪያቤታችን ግዥውን የሚፈፀመው በጥራትም ሆነ በዋጋ ብቁ መሆናቸውን አረጋግጦ የመረጣቸውን ይሆናል

1.1 የተፈላጊ ዕቃዎች ዝርዝር አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ ላይ ተመልክቷል ።

2. የመወዳደሪያ ሃሳቡ በታሸገ ኢንቨሎፕ ውስጥ ሆኖ ለግዢ ፈጻሚው መስሪያ ቤት ቢሮ ቁጥር 12 መድረስ አለበት :: የመወዳደሪያ ሃሳቡ በ 09/06/2018 ዓ.ም 3:30 ሰዓት ይከፈታል ፡

2.1 የዕቃዎች ማስረከቢያ ቦታ በትግራይ ክልል ግብርናና ተፈጥሮ ሃብት ቢሮ ሆኖ ማስረከቢያ ጊዜው ግዢው ከታዘዘበት ቀን ጀምሮ በ 15 አስራ አምስት ቀናት ውስጥ ይሆናል።

3 አቅራቢዎች ጠቅላላ ዋጋውን በቁጥርና በፊደል መጻፍ አለባቸው :: በቁጥርና በፊደል : በተገለፀው የዋጋ መጠን መካከል አለመጣጣም ካለ በፊደል የተገለፀው ተቀባይነት ይኖረዋል :: በነጠላ ዋጋ እና በጠቅላላ ዋጋ መካከል ልዩነት ካለ ነጠላ ዋጋው ተቀባይነት ይኖረዋል ።

3.1 አቅራቢዎች በእያንዳንዱ የዕቃ ዝርዝር ማቅረቢያ ሰንጠረዥ ውስጥ የዕቃውን አይነትና ብዛት፣ነጠላ ዋጋ እና ጠቅላላ ዋጋውን መሙላት እንዲሁም ቀን ፣ ፊርማና የድርጅቱን ማህተም ማስፈር ይገባቸዋል ::

3.2 ማንኛውም ተጫራች ከጨረታ መዝጊያ ቀንና ስዓት በኋላ የቀረበ የዋጋ ማቅረቢያው ሰነዱን የመወዳደሪያ ሃሳብ ማስገባትይኖርበታል። ከጨረታ መዝጊያ ቀንና ስዓት በኋላ የቀረበ የዋጋ ማቅረቢያው ሰነድ የመወዳደሪያ ሃሳብ ተቀባይነት የሌለው ሲሆን ኤንቨሎፑ ሳይከፈት ለተጫራቶች ተመላሽ እንዲሆን ይደረጋል።

4.1 ለአሸናፊ ተጫራቶች ዕቃውን ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል በውለታመሰረት አጠናቆ ማስገባቱና ማጠናቀቁ ከተረጋገጠ በኋላ ቢበዛ በሰባት ቀናት ውስጥ ሙሉ ክፍያ ይከፈለዋል ።

4.2 የመወዳደሪያ ሀሳብ ማቅረቢያ ቋንቋው በአማርኛ ነው ::

5 ዕቃዎቹ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች /Specification/ ተያይዟል ::

5.1 አሸናፊው አቅራቢ የሚለየው ለእያንዳንዱ ዕቃ ያቀረበው /Item by Item / ዝቅተኛ ዋጋ መሰረት ይሆናል

6 የመወዳደሪያ ሂሳቡ ዋጋ የሚቀርበው በኢትዮጵያ ብር ይሆናል ::

7 የጨረታ ማወዳደሪያው በሚከተለው መሰረት ይሆናል ፡

• የቀረቡት ዕቃዎች ቴክኒካል መስፈርቶቹን ያሟሉ መሆናቸው ይረጋገጣል ::

■ በቀረበው ዋጋ ላይ የሂሳብ ድምር ስህተት ካለ እንዲታረም ይደረጋል ::

ውድድሩ የሚካሄደው እና ዝቅተኛ ዋጋ አቅራቢው የሚለየው በታረመው ዋጋ መሰረት ይሆናል ::

8 ጨረታው የቴክኒክ መስፈቱን ካሟሉት አቅራቢዎች መካከል ዝቅተኛ ዋጋ ላቀረበው ተጫራች አሸናፊው ይደረጋል ::

9 ተጫራቶች የሚከተሉት ሰነዶች ከጨረታ ሰነዱ ጋር ማያያዥ ይኖርባቸዋል ::

➢ በዘርፉ የታደሰ ንግድ ፍቃድ ኮፒ

➢ የግብር ምዝገባ ቁጥር ወይም የግብር ከፋዩን መለያ ቁጥር ኮፒ

10 መስሪያ ቤታችን የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው ::